## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የተማሪዎችና የመምህራን የድጋፍ ዘመቻ

**እየሩስ ተስፋዬ**



ኢትዮጵያ አሁን ከገባችበት የሕልውና ጦርነት እንድትወጣ የትምህርቱ ዘርፍ ያልተቋረጠ ድጋፉን ለማድረግ በተለያዩ ግንባሮች በመዝመት የድርሻውን እየተወጣ እንደሆነ ይታወቃል። የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤ ከኅዳር 27 እስከ ታህሳስ 03 ቀን 2014 ባሉት ቀናት ውስጥ ትምህርት ቤቶች ለአንድ ሳምንት ዝግ ሆነው የትምህርት ማኅበረሰቡ፤ ሰብል በመሰብሰብና በተለያዩ መንገዶች ድጋፉን እንደሚያደርግ ውሳኔ ማስተላለፋቸውን ተከትሎ፤ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎችና መምህራን በተለያዩ ማኅበራዊ አገልግሎቶች ላይ ለመሳተፍ ችለዋል።

ውሳኔውን ተከትሎም የዘማች ቤተሰቦች ሰብል ለመሰብሰብ ለሚሰማሩ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በአበበ ቢቂላ ስታዲየም በተካሄደው የሽኝት መርሐግብር ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ የጸጥታ ኃይሉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ያለምንም እንከን መከታተል እንዲችሉ ለማድረግ እየተዋደቀ ይገኛል። ተማሪዎች ከዚህ በፊት የ100 ሚሊዮን ብር ድጋፍ በማድረግ ኢትዮጵያ አትፈርስም ብለው አሻራቸውን ማኖራቸውም የሚያኮራ ነው።

እንዲሁም ይህ ዘመቻ በምግብ ራሳችን ለመቻል፤ የዘማች ቤተሰቦችን ሰብል ለመሰብሰና ሕይወቱን እየሰጠ ላለው ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት፣ ለልዩ ኃይሎችና ለሚኒሻዎች ደም በመለገስ ኢትዮጵያ እንደማትፈርስ ልንነግራቸው ጭምር ነው በማለት የገለጹት ከንቲባዋ ፤ ‹‹ይሄ የሚረሳ ታሪክ አይደለም። የእኛ ትውልድም አዲስ ታሪክ እየሠራ ነው።››ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ በበኩላቸው፤ በሰብል ስብሰባ መርሐ ግብሩ ላይ ከሦስት ሺ በላይ ተሳታፊዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ ከዚህ በኋላም ቢሆን የትምህርት ዘርፉ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን የሕልውና ትግሉ በድል እንዲጠናቀቅ የበኩሉን ኃላፊነት እንደሚወጣ አስታውቀዋል።

በዚህ ዘመቻ የሰብል ስብሰባ መርሐ ግብሩ ከተከናወነባቸው አካባቢዎች በኦሮሚያ ልዩ ዞን በረከ ቀበሌ "ዘመቻ በትምህርት ልማት ግንባር" መሪ ሐሳብ የተካሄደ ሲሆን በፕሮግራሙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቀነዓ ያደታ፣ የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ ተወካዮች፣ አባ ገዳዎችን ጨምሮ የትምህርት አመራሮችና ባለሙያዎች መሳተፋቸውን ከአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

የከተማዋ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ የሰብል ስብሰባ መርሐ ግብሩን ባስጀመሩበት ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት ይህ የተቀደሰ አላማ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከበር በየጦር ግንባሩ ተጋድሎ በማድረግ ላይ የሚገኙ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ቤተሰቦችን ሰብል በመሰብሰብ ከጎናቸው በመሆን የሚረጋገጥበት ተግባር መሆኑን ሲገልጹም፤‹‹ዘመቻው ተባብረንና ተጋግዘን የአገራችንን ልማትና ብልጽግና እንደምናረጋግጥ ሁነኛ ማሳያ ነው።›› በማለት ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ልዩ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ ወይዘሮ ዝናሽ አቤቤ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተውጣጡ መምህራንና ተማሪዎችን ጨምሮ የተለያዩ የትምህርት ማኅበረሰብ አካላት በልዩ ዞኑ ተገኝተው የዘማች ሚሊሻ ቤተሰቦችን ሰብል በመሰብሰብ ላሳዩት አጋርነት በልዩ ዞኑና በዘማች ሚሊሻዎች ስም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ዘመቻውን ከግብ ለማድረስም ተማሪዎች፣ መምህራንና የትምህርት ማኅበረሰቡ በተለያዩ አካባቢዎች ሰብል በመሰብሰብ፣ ደም በመለገስ የዘማች ቤተሰቦችን በማገዝና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶችን በማከናወን ለአገራቸው በሚችሉት መንገድ መልካም አሻራቸውን ማኖር ችለዋል። የጤፍና በቆሎ አጨዳ፣ የጥጥ ለቀማም በሰሞኑ የውሎ ዘመቻው ላይ በስፋት የተሠራባቸው ሥራዎችም ናቸው። በጎ አድራጊ ተማሪዎችና መምህራን ማኅበራዊ አገልግሎቶች በተለያዩ አካባቢዎች በመገኘት ለተፈናቀሉ ወገኖች የአልባሳት ድጋፍ ሲያሰባስቡና ስንቅ በማዘጋጀትም የድርሻቸውን ከመወጣት አልተቆጠቡም።

ምንም እንኳን ለአንድ ሳምንት ትምህርት ቤቶች ይዘጉ እንጂ ፤ ተማሪዎችና መምህራን ደም ከመለገስ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም የተተከሉ ችግኝ በመንከባከብ የትምህርት ዘርፉ በአገራዊ ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆኑን በሠሯቸው በጎ ሥራዎች ማስመስከር ችለዋል።

በአጠቃላይ የትምህርቱ ማኅበረሰብ ለአገር መከላከያ ሠራዊት፣ ለፀጥታ ኃይሎችና ተፈናቃዮች የተለያዩ ድጋፎችን ከማድረግ በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎች በኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ያለውን የዓለም አቀፍ ተፅዕኖን ለመቃወም የተጀመረውን የ‹በቃ›ን ወይም "No more" ዘመቻንም ከድጋፋቸው ጎን ለጎን ድምጻቸውንም ማሰማት ችለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተማሪዎች ላከናወኑት ማህበራዊ አገልግሎት ምስጋና ማቅረባቸውም ይታወሳል።

ለአንድ ሳምንት በዘመቻው ምክንያት ትምህርት ቤቶች ይዘጉ እንጂ የማካካሻ ትምህርት ይሰጣል።

## ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

# የተሽከርካሪዎች ሰሌዳ ማምረትና ማሰራጨት




ቀደም ሲል በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ይታተምና ይሰራጭ የነበረው የተሽከርካሪዎች ሰሌዳ ባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ በአዋጅ ፈርሶ መብትና ግዴታዎቹ ለፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር መተላለፉ ይታወሳል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም ይህንን የተሽከርካሪዎች ሰሌዳ የማተምና የማሰራጨት ሥራ ለፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በውክልና ሰጥቶ ድርጅታችንም ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል።

በመሆኑም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል የተሽከርካሪ ሰሌዳ ለማሳተም ስትፈልጉ በቅድሚያ ከድርጅታችን ጋር ውል መግባት ይጠበቅባችኋል። በመቀጠልም የምትፈልጉትን የታርጋ ዓይነትና ብዛት በዝርዝር በመላክ አሳትማችሁና ክፍያውን ፈፅማችሁ ለደንበኞቻችሁ ማደል ትችላላችሁ።፡ በዚህ አጋጣሚ ክልሎችም ሆነ ከተማ አስተዳደሮች የምትፈልጉትን ያህል የተሽከርካሪ ሰሌዳ በአጭር ጊዜ አትመን ለማስረከብ እንደምንችልና ምንም ዓይነት የጥሬ ዕቃ ችግር የሌለ መሆኑን እንገልፃለን።

የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የማንኛውም ዓይነት የተሽከርካሪ ሰሌዳ የማተምና የማሰራጨትን ኃላፊነትን ከፌዴራል ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ ሚኒስቴር በውክልና ተረክቦ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን፤ ሥራውን የተቀላጠፈና ከብልሹ አሠራር የፀዳ ለማድረግ ሲባል የጠፋ የተበላሸና ምትክ ሰሌዳ የሚፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጡበት የትራንስፖርት ቢሮ በኩል መስተናገድ እንዲችሉ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል። በመሆኑም አገልግሎቱን የምትፈልጉ ደንበኞች ሰሌዳውን ባወጣችሁበት ቢሮ በሕጉ መሠረት አስፈላጊውን መረጃ ይዛችሁ በመቅረብ አገልግሎቱን ማግኘት ትችላላችሁ።

ድርጅታችን ከየትራንስፖርት ቢሮዎቹ በሚደርሰው የሥራ ትዕዛዝ መሠረት ሰሌዳዎችን በብዛትና በዓይነት አትሞ ለየቢሮዎች ለማሰራጨት እንደሚችልና ምንም ዓይነት የጥሬ ዕቃ ችግር የሌለበት መሆኑን ለክቡራን ደንበኞቹ ያሳውቃል። በግለሰብ ደረጃ የሚመጡ ማንኛውንም ዓይነት የሰሌዳ ጥያቄ የማናስተናግድ መሆኑን እንገልፃለን።

የተሽከርካሪ ሰሌዳ አገልግሎት ለመስጠትና የተከማቸውን ሥራ ለማቃለል የሰውና አስፈላጊ የሚባሉ ማሽነሪዎችን በማደራጀት ወደ ሥራው ተገብቷል። ቀድም ብሎ ለተሽከርካሪ ሰሌዳ ሕትመት ይከፈል የነበረው ገንዘብ ላይ ማሻሻያ ተደርጓል። የመጀመሪያው ለመኪና ሰሌዳ ይደረግ የነበረው ክፍያ ቀደም ብሎ በነበረው የገበያ ሁኔታ የተተመነ ስለነበር ማሻሻል አስፈልጎታል።

የመኪና ሰሌዳ ማምረት ላይ የሚሳተፉ በርካታ ሠራተኞች ይገኛሉ። ሠራተኞቹ ቀደም ብለው በትራንስፖርት ባለስልጣን ሥር ይሰሩ ነበር። ለሠራተኞቹ የተሻለ ደመወዝ መክፈል አስፈልጓል። በተለይ ደግሞ የውጪ ምንዛሪውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ክፍያ እንዲሆን በማስፈለጉ ነው። ለሰሌዳ ምርት የሚሆኑት ማሽነሪዎችና ጥሬ እቃዎቸው ሙሉ ለሙሉ የሚገቡት ከውጪ ነው። የሰሌዳ ቁጥር ፈላጊ በተለይ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ሕጉን ጠብቀው ልከው የተመረተ ሰሌዳዎች ይገኛሉ። ይህን ሰሌዳ በፍጥነት ወስደው ለሕዝብ ማድረስ አለባቸው።

በድርጅቱ እስካሁን ያጋጠመ ምንም አይነት የጥሬ እቃ እጥረት የለም። በተጨማሪም ምንም ዓይነት የሰሌዳ ሕትመት እጥረት ባለመኖሩ ሁሉም ትራንስፖርት ቢሮዎች ፍላጎታቸውን ጠይቀው በተባለው ጊዜ ሰርቶ ለማስረከብ ዝግጅት ተጠናቋል። በቅርብ ይህንን ሥራ የጀመረው ድርጅቱ በአዲሱ አሰራር መሠረት ከክልል ቢሮዎች ጋር በመተባበር የተለያዩ ኮድ ያላቸውን ከ10 ሺህ በላይ የተሽከርካሪ ሰሌዳዎችን ሰርቶ አጠናቋል።